የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

# የጤና ተግባቦት መርጃ መሳሪያዎች አዘገጃጀት መመሪያ

# የጤና ተግባቦት መርጃ
# መሳሪያዎች አዘገጃጀት መመሪያ

# መቅድም

ባለፉት ሁለት ዐሥርት ዓመታት ኢትዮጵያ መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ሽፋንን በማሳደግ እና ለአብዛኛው ኅብረተሰባችን በማዳረስ አበረታች ዕድገት አስመዝግባለች፡፡ ይህም መንግሥት፣ የልማት አጋሮችና ማኅበረሰቡ ተቀናጅተው በሰሩት ያልተቆጠበ ጥረትና መጠነ ሰፊ ኢንቨስትመንት የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን እና መሠረታዊ የጤና ክብካቤ አሃድን ማስፋፋት በመቻሉ የተገኘ ውጤት ነው፡፡

የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን በመተግበሩ እንዲሁም እንደ እናቶችና ሕጻናት ጤና፣ የቲቢ ምርመራና ሕክምና፣ የቤተሰብ ዕቅድ የመሳሰሉትን ዋና ዋና የጤና ፕሮግራሞች ከክፍያ ነጻ በማድረጉ የጤና አገልግሎቱን ለኅብረተሰቡ ይበልጥ ተደራሽ አድርጎታል፡፡ ኢትዮጵያ ከጤና ጋር የተገናኙትን አብዛኛዎቹን የምዕት ዓመቱን የልማት ግቦች አሳክታለች፡፡ እነዚህም ግብ-4 (የሕጻናትን ሞት መቀነስ)፣ ግብ-5 (የእናቶችን ሞት መቀነስ)፣ ግብ-6 (ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን፣ ቲቢን እና ወባን መቆጣጠር) ናቸው፡፡ ከዚህም በላይ ሀገራችን በአዲሶቹ የዘላቂ ልማት ግቦች ላይ አርአያነት ያለው ስኬት ለማስመዝገብ በሚያስችላት አበረታች ሁኔታ ላይ ትገኛለች፡፡

ይህ አበረታች ዕድገት ቢመዘገብም ተላላፊ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች አሁንም ዋነኛ የጤና ችግሮች ሆነው ይገኛሉ፡፡ ከተደረሰው ከፍተኛ የጤና አገልግሎት ሽፋን በተቃራኒው የሚታየው ዝቅተኛ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት ዛሬም ዋነኛው ተግዳሮት ነው፡፡ ይህም ከባህል ጋር የተያያዙ ጉዳዮች፣ የባለሙያዎች አመለካከትና ብቃት፣ የተገልጋዮች ምርጫ እና የጤና አገልግሎት የመሻት ጠባይን በቤተሰብ እና በማኅበረሰብ ደረጃ በመዳሰስ የሚዘጋጅ መፍትሔ ያስፈልገዋል፡፡

የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ያለውን የጤና እና የጤና አገልግሎት ተጠቃሚነት ሁኔታ ለማሻሻል ሀገር አቀፍ የጤና ማበልጸግ እና ተግባቦት ስትራቴጂ (2008/09 ዓ.ም - 2012/13 ዓ.ም) በማዘጋጀት ወደ ስራ ገብቷል፡፡ ይህን ስትራቴጂ ከማስፈፀም አንፃርም የተለያዩ የማስፈፀሚያ መመሪያዎች ማዘጋጀትና እንዲተገበሩ አስፈላጊውን ክትትልና ግምገማ ማድረግ አንዱና ቁልፉ ተግባር ነው፡፡

የተለያዩ የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሳረያዎች( የህትመትም ሆነ የኤሌክትሮኒክስ ) ዝግጅት ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲዘጋጁ ይህ የአፈፃፀም መመረያ ተዘጋጅቷል፡፡ በመሆኑም በፌደራል፣ በክልልም ሆነ በተዋረድ ያሉ ፈፃሚ አካላትም ሆነ አጋር አካላት ማንኛውንም የጤና አጠበበቅ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ሲያዘጋጅ ይህን መመሪያ መሰረት በማድረግ እንዲሆን ጥሪዩን አስተላልፋለሁ፡፡

ከበደ ወርቁ (MD, MPH)
ሚኒስትር ዴኤታ
የኢፌድሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

# ማውጫ


 መግቢያ 1

የመመሪያው ዓላማ 2

የማኅበራዊና የባህርይ ለውጥ ተግባቦት 2

ሃገር አቀፍ የጤና ማበልጸግና ተግባቦት ስልት አተገባበር ላይ ተግባራዊ የሆነ ሞዴል 3

የጤና ተግባቦት መርጃ መሳሪያዎች አዘገጃጀት ንድፈ ሃሳብ 5

ዳሰሳ ማድረግ 6

የማስፈፀሚያ ስትራተጂ 7

መርጃ መሳሪዎችን ማዘጋጀትና ቅድመ ሙከራ ማድረግ 8

የትግበራና ክትትል ሂደት 14

# አባሪዎች


የማኅበራዊ ባህርይ ለውጥ የተግባቦት ንድፈ ሐሳቦች 16

የተመረጡ  የብዙኃን መገናኛ  አይነቶች ጥንካሬና ድክመት 20

የቅድመ ሙከራ የቡድን ውይይት መምሪያ 24

የተግባቦት መልዕክቶችን ለማዘጋጀት የሚረዳ ንድፍ 28

ጥራት ያለው የማህበራዊ የባህርይ ለውጥ ተግባቦት መልዕክቶችን ለማዘጋጀት የሚረዳ መዘርዝር 33

የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የስርጭትና የትግበራ ክትትል ለማካሄድ የተዘጋጀ ፈጣን መዘርዝር 36

# ምስጋና

የዚህ መመሪያ ዝግጅት የተሳካ ይሆን ዘንድ የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ድርጅቶች እና የወከሏቸዉን ባለሙያዎች ይህን መመሪያ በማዘጋጀት  እና በማጠናቀቅ አሁን ያለበት ደረጃ እንዲደርስ ላበረከቱት ያልተቆጠበ አስተዋጽኦ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

- BBC Media Action
- Integrated Family Health Program (IFHP)
- Jhpiego
- John Hopkins Center for Communication Programs (CCP)
- John Snow Inc./L10K
- Save the Children
- United Nations Children's Fund (UNICEF)
- World Health Organization (WHO)

# 1. መግቢያ

ባለፉት አስርት ዓመታት ሀገራችን በጤናው ዘርፍ ከፍተኛ ለውጥ አስመዝግባለች፡፡ ነገር ግን አሁንም የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በተላላፊና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች እንዲሁም በተለያዩ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች እየተጠቁ ይገኛሉ፡፡ አብዛኛዎቹ የጤና ችግሮች ታቅደው በሚተገበሩ የጤና ተግባቦት ስራዎች መከላከል የምንችላቸው ናቸዉ፡፡ የኢትዮጵያ መንግስትም በሽታን ከመከላከልና መቆጣጠር አንጻር ሁሉን አቀፍ የጤና ፖሊሲ እና ስትራቴጅ ቀርጾ የህብረተሰቡን የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ለማረጋገጥ እየሰራ ይገኛል፡፡

የጤና ማበልጸግና ተግባቦት በጤና አገልግሎት ስርዓት ውስጥ ረጅም ታሪክ ያለዉ ሲሆን በአሁኑ ወቅትም በጤና ኤክስቴንሽን እና መሰረታዊ የጤና አገልግሎት ዳይሬክቶሬት አስተባባሪነት ትኩረት ተሰጥቶት እየተተገበረ ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሃገር አቀፍ የጤና ማበልጸግና ተግባቦት ቴክኒካል ወርኪንግ ግሩፕ ተቋቁሞ የተለያዩ የጤና ማበልጸግና ተግባቦት ስራዎችን በመደገፍ ላይ ይገኛል፡፡ በቴክኒካል ወርኪንግ ግሩፑ ድጋፍም ሃገር አቀፍ የጤና ማበልጸግና ተግባቦት ስትራቴጅ ተዘጋጅቷል፤ ስትራቴጅዉ የሃገሪቱን የጤና ስርዓት ለዉጥ ማዕከል ያደረገ እና በአሁኑ ጊዜ ያሉትን ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እንዲሁም የጤና ኤክስቴንሽንና የጤና ልማት ሰራዊት አፈጻጸም ላይ ትኩረት ያደረገ ነዉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አሁን ካሉት የመገናኛ ብዙሃን ( የህትመትና ኤሌክትሮኒክስ) እንዲሁም አዳዲስ የተግባቦት የመረጃ መለዋወጫ መንገዶች መስፋፋት ጋር የተያያዘ ነዉ፡፡

ይህ መመሪያ የጤና ማበልጸግና ተግባቦት ስትራቴጅዉን ለመተግበርና ወጥነት እና ጥራት ያላቸዉ የጤና ተግባቦት መርጃ መሳሪያዎችን እንዲዘጋጁ ለማድረግ ይረዳል፡፡ በጤናዉ ዘርፍ ያሉትን የጤና ፕሮግራሞች መሰረት በማድረግ የጤና ተግባቦት መርጃ መሳሪያዎች ደረጃ በደረጃ እንዴት መዘጋጀት እንደሚችሉ አቅጣጫ ያሳያል፡፡

## 1.1. የመመሪያው ዓላማ

- ተመሳሳይነት እና ወጥነት ያላቸው የጤና ተግባቦት መርጃ መሳሪያዎች አዘገጃጀት ስርዓት እንዲኖር ማድረግ
- የጤና ማበልፀግ እና ተግባቦት መልዕክቶች እና መርጃ መሳሪያዎች ወጥ የሆኑና የማይቃረኑ(የሚጣጣሙ) እንዲሆኑ ማድረግ

## 1.2. የማህበራዊ ባህርይ ለውጥ ተግባቦት

የማህበራዊ ባህርይ ለዉጥ ተግባቦት ማለት ለባህርይ ለውጥ መነሻ የሆኑ ነጥቦችን ተደራሽ ለማድረግ ሳይንሳዊ የሆነ ጽንሰ ሃሳብና ጥናትን መሰረት ያደረገ ሂደትን በመከተል፣ ስትራቴጂ በመንደፍ እና በመተግበር የግለሰብ፣ የማህረሰብና የማህበራዊ ባህርይ ለዉጥ እንዲመጣ የሚያስችል ስልት ነዉ፡፡

የለዉጥ መነሻ ነጥቦች ሲባል አንድ ባህርይ ለመለወጥ የሚጀመርበት ሂደት ሲሆን በሂደት ወደ ዘላቂ ለዉጥ ይደርሳል፡፡ ይህም የለውጥ መነሻ ነጥብ ወደ ዘላቂ የባህርይ ለውጥ ለመድረስ እና አዲሱን ባህርይ ጠብቆ ለመቆየት ተፈጥሮአዊ በሆኑ ክስተቶች ወይም ለዉጥ ለማምጣት የሚያስችል የፖለቲካ ቁርጠኝነት ድጋፍ እና ግፊት ይደረግባቸዋል፡፡

በአለፉት አመታት የጤናና የልማት ፕሮግራሞች የሰዎች ባህርይ ላይ ያላቸዉ ግንዘቤና አመለካከት እየተቀየረ በመምጣቱ በግለሰብ የባህርይ ለውጥ ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ ዘለቄታዊ የሆነ የማህበራዊ ለዉጥንም ለማካተት ተችሏል፡፡

የማህበራዊ የባህርይ ለዉጥ ተግባቦት ሂደት ለለውጥ መሰረት በሆኑትን የለውጥ መነሻ ሃሳቦች ላይ በተለያዩ ደረጃዎች ማለትም ግለሰባዊ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ሁኔታዎችን በመተንተን ዘላቂ ለውጥ እንዲመጣ ያስችላል፡፡

### *የማህበራዊ ባህርይ ለዉጥ ተግባቦት መገለጫዎች*

1. የግለሰብና የማህበረሰብ የባህርይ ለዉጥ ለማምጣት አሳታፊ የሆነ፣ ጥናትን መሰረት ያደረገ፣ የታቀደ የስልት ሂደት ይከተላል
2. ሁሉን አቀፍ ማህበራዊ ጽነሰ ሃሳብና ሞዴል ይጠቀማል
3. የሚከተሉትን ቁልፍ ስልቶች ይጠቀማል
   - **አድቮኬሲ፡-** የፖለቲካ እና የማህበረሰብ አመራሮችን ቁርጠኝነት ለማሳደግ እንዲሁም የተለያዩ ግብዓቶችን እንዲመደቡ ለማድረግ የምንጠቀምበት ስልት ነው

- **ማህበራዊና የማህበረሰብ  ንቅናቄ፡**- ሰፊ ተሳታፊዎችን በማካተትና ንቅናቄ በማድረግ ህብረትና ባለቤትነትን ለማምጣት የሚያስችል ስልት  ነዉ
- **የባህርይ ለዉጥ ተግባቦት፡**- ለተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እዉቀት፣ አመለካከትና ትግበራ ለማምጣት የሚተገበር ስልት  ነዉ

*የማህበራዊ ባህርይ ለዉጥ ተግባቦት  መሰረታዊ መርሆች*

1. ሳይንሳዊ ስልቶችን ይከተላል
2. ፕሮግራም ለመንደፍ ጥናቶችን መሰረት ያደርጋል
3. ማህበራዊ ሁኔታዎችን ያማከላል
4. በተመረጡ ወይም በተወሰኑ ታላሚዎች ላይ ያተኩራል
5. ለዉሳኔ ጽነሰ ሃሳቦችን እና ሞዴሎችን ይጠቀማል
6. ማህበረሰቡን እና አጋሮችን ያሳትፋል
7. አላማ በማስቀመጥ ወጪ ቆጣቢነትን ከግምት ያስገባል
8. በየደረጃው ተደጋጋፊነት ያላቸዉን መርጃ መሳሪያዎችንና ተግባራትን ይጠቀማል
9. ድርጊትን መሰረት ያደረገ እና አነቃቂ ስልቶችን ይጠቀማል
10. በየደረጃው ጥራትን ያረጋግጣል

## 1.3. በጤና ማበልጸግና ጤና ተግባቦት ስትራቴጅ የተመረጠ የጤና ተግባቦት ሞዴል

የጤና ተግባቦት ተግባራትን ለመቅረጽ፣ ለመተግበር እና የጤና ችግሮችን እንዲቀንሱ ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ የማህበራዊ ባህርይ ለዉጥ ተግባቦት ጽንሰ ሃሳቦችና ሞዴሎች አሉ (አባሪ 1. ተመልከቱ)፡፡  እነዚህ ጽነሰ ሃሳቦችና ሞዴሎች  ጤናማ የሆኑ ባህርያት የሚያጎለብቱ ተግባራትን እንዴት መንደፍ እንደሚቻል አግባብነት ያለው ሂደትን ያሳያሉ፡፡ በዋናነትም የማህበራዊ ባህርይ ለዉጥ ተግባቦት  ተግባራትን ለማቀድ የሚያግዙ ቢሆኑም የሰዎች ባህርይ  በተለያዩ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሁኔታዎች ይወሰናል፡፡ ስለዚህ ማንኛዉም በጽነሰ ሃሳብ እና በሞዴል በመመራት የተዘጋጀ የማህበራዊ ባህርይ ለዉጥ ተግባቦት ፕሮግራም የተለያዩ በሰዎች ባህርይ ላይ ተጽዕኖ ሊያደርጉ የሚችሉ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ ዉስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡






*Figure 1: Determinants of health – Socio- Ecological Model*
*Source: Dahlgren & Whitehead, 1991*

# 2. የጤና ተግባቦት መርጃ መሳሪያዎች አዘገጃጀት ንድፈ ሃሳብ

ማንኛዉንም አይነት የጤና ተግባቦት መርጃ መሳሪዎችን ለማዘጋጀት ከማህበራዊ ባህርይ ለዉጥ ተግባቦት መሰረታዊ መርሆች በተጨማሪ ሳይንሳዊ ስልት እና አሳማኝ ንድፈ ሃሳብ መከተል ያስፈልጋል፡፡

የጤና ተግባቦት መርጃ መሳሪያ ይዘት በራሱ የተወሰነ ሊሆን ይችላል፤ ንድፈ ሀሳብ አዳዲስ የጥናት ዉጤቶችን መሰረት በማድረግ እንደ አካባቢያዊ ነባራዊ ሁኔታ መለወጥ ይችላል፡፡



## 2.1. ዳሰሳ ማድረግ

አንድን የጤና ተግባቦት መርጃ መሳሪያ ለማዘጋጀት የመጀመሪያዉ ተግባር  መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ በቂ ግንዛቤ (በጤና ችግሩ፣ በማህበረሰቡ፣ በፖሊሲ እና ፕሮግራሞች ዙሪያ) ማግኘት ነዉ፡፡ ስለዚህ ማንኛዉም አይነት የጤና ተግባቦት ፕሮግራም ዝግጅት የሚጀምረዉ ጥልቀት ያለው የነባራዊ ሁኔታ፣ የታላሚዎችና የፕሮግራም ትንተና በመስራት ነው፡፡

*የነባራዊ ሁኔታ ትንተና*

የነባራዊ ሁኔታ ትንተና የሚካሄደው  በጤና ተግባቦት ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮችን ለማወቅና  ክፍተቶችን ለመለየት ነው ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የችግሩን ስፋትና መጠን እንዲሁም መሻሻል የሚችሉ ባህርያትን ለይቶ በመረዳት ለመቅረፍ ነው፡፡

በዳሰሳው ወቅት ያሉትን ነባራዊ ሁኔታዎች ማለትም የጤና ፕሮግራሞችንና የስነ-ሕዝብ መረጃዎችን ማየት ያስፈልጋል፡፡ የተዳሰሱ መረጃዎች በቂ ሆነዉ ካልተገኙ ተጨማሪ የዳሰሳ ጥናቶች መታሰብ ይኖርባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ የነባራዊ ሁኔታ ትንታኔ የጋራ የሆነ እይታ እና እዉነታ እንዲኖር ያግዛል፡፡

*የታላሚ ልየታ*

ማንኛዉም አይነት የጤና ተግባቦት ፕሮግራሞች ታላሚዎችን ለይቶ የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡ ታላሚ ልየታ ማለት  በዳሰሳ ጥናት የተለዩ ክፍተቶችን መሰረት በማድረግ ታላሚዎችን በመለየት የሚዘጋጀው መልዕክት እንዲሁም የሚተላለፍበት መንገድ ለታላሚዎች እንዲስማማ ማድረግ ነው፡፡

> የታላሚ ልየታ ማድረግ የሚስፈልገው፡-
> የተለየዩ ሰዎች የተለያየ የጤና የመረጃ ፍላጎት ስላላቸዉና ያለዉን ግብዓት በአግባቡ ለመጠቀም ስለሚያስችል ነዉ፡፡ በተቻለ መጠን ታላሚዎችን  በሚከተሉት  ዋና ዋና መገለጫዎች ማየት ያስፈልጋል። ይኅውም በስነሕዝብ፤መልክዓ -ምድራዊና ስነ-አዕምሮአዊ  ሁኔታ  ወዘተ

ታላሚ ከተለዩ በኋላ

- ታላሚዎች እንዲተገበሩት የሚፈለገዉን ባህርይ በግልጽ መለየት
- ታላሚዎችን ተመሳሳይ የሚያደርጋቸዉን መገለጫዎች(ስነ ህዝብ፤ ስነ አዕምሯዊ የመገናኛ ብዙሃን ፍላጎት ) መለየት
- መሰናክሎችን እንዲሁም የሚፈለገው ባህርይ እንዲተገበር የሚያመቻቹና ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎችን መለየት
- ታላሚዎች የሚፈለገዉን ባህሪይ ቢተገብሩ ሊያገኙ የሚችሉትን ጥቅም መለየት

*የፕሮግራም ትንተና*

የፕሮግራም ትንተና ማካሄድ ዉጤታማነትን ለመጨመር ያስችላል፡፡ የጤና ተግባቦት መርጃ መሳሪያዎች በሚዘጋጅበት ወቅት፡-

1. የፕሮግራሙን ጥንካሬ፣ ድክመት፣ የመልካም አጋጣሚና ስጋቶች ትንተና ማካሄድ (SWOT analyisis)
2. በወቅቱ ያሉ የጤና ፕሮግራሞችንና ፖሊሲዎችን ዳሰሳ በማድረግ ለፕሮግራሞቻችን አጋዥ የሆኑትን አገልግሎት ሰጭዎችና አቅርቦቶችን መለየት
3. የተግባቦት ስራዉን ሊያግዙ የሚችሉ፤አቅም ያላቸውና እንዲሁም የትግበራ ስራውን በቋሚነት የሚደግፉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ፤ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ሊያደርጉ የሚችሉ ሃላፊዎችን፤ፍላጎት ያላቸው ማዕከላትና የንግድ ድርጅቶችን መለየት
4. የሚዲያዎችን ለታላሚ ተደራሽነትና አዋጭ ሁኔታዎችን መለየት እንዲሁም የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ታላሚዎች ለሚዲያው ያላቸውን ተደራሽነትና ፍላጎት መለየት

## 2.2. የማስፈጸሚያ ስትራቴጅ

ማንኛዉም አይነት የጤና ተግባቦት መርጃ መሳሪያዎች ከመዘጋጀታቸዉ በፊት ግልፅ የሆነ የማስፈጸሚያ ስትራቴጅ ሊኖራቸወ ይገባል፡፡ ስትራቴጅው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ተግባራት ላይ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡ በዋናነትም የሚዲያ ምርጫን በምናቅድበት ወቅት የታላሚውን የሚዲያ ፍላጎት፣ የተለያዩ ሚዲያዎች ጠንካራና ደካማ ጎን፣ መልዕክቶች የሚተላለፉበትን ጊዜና ወቅት፣ አከባቢያዊ ሁኔታዎች፣ የሚተላለፈው መልዕክትና ማስተላለፊያ መንገዶች መጣጣማቸውን እና ለፕሮግራሙ ማስፈፀሚያ ያለውን ግብዓት መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል (አባሪ 2. ይመልከቱ)

- የተግባቦቱ ዓላማዎች ምንድን ናቸው? (ዓላማዎቹ ውስን፤መለካት የሚችሉ፤አግባብነት ያላቸው፤ትክክለኛ፤በጊዜ የተገደቡ መሆን አለባቸው)
- እንዲተገበር የሚፈለገው ባህርይ ምንድን ነው?
- ታላሚው እንዲተገብር  የሚፈለገውን ባህርይ በማምጣቱ የሚያገኘው ጥቅም ምንድን ነው?
- የባህርይ ለወጥ ለማምጣት ምን አይነት ዘዴዎች እንጠቀማለን? (ጠቃሚ የሆነዉን የባህሪይ ለዉጥ ጽነሰ ሃሳብ መምረጥ)

- የብዙሃን መገናኛ እቅድ በሚታቀድበት ወቅት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መመለስ አለባቸው
    1. ምን ያክል ሰዎችን በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን መድረስ ይቻላል?
    2. በየትኛዉ የብዙሃን መገናኛ መልዕክቶቹ መተላለፍ አለባቸው?(የተለያዩ ሚዲያዎችን መጠቀም ውጤታማ ያደርጋል)
    3. መልዕክቶቹ ለምን ያክል ጊዜ መተላለፍ አለባቸዉ?
    4. መልዕክቶቹን ለማዘጋጀትና ለማሰራጨት ምን ያክል ገንዘብ ያስፈልጋል?
- የባህሪይ ለዉጥ ሊያመጡ የሚችሉ ዋና ዋና ተግባራት ምንድን ናቸው?
- መልዕክቶችን የማሰራጨት(የማስተላለፍ) ስርዓቱ ምን መምሰል አለበት?
- የክትትልና ግምገማ እቅድ ምን መምሰል አለበት?
- ያለን የገንዘብ መጠንና ስራውን ለማከናወን የወጣው መርሃ-ግብር ምን መምሰል አለበት?

## 2.3. መርጃ መሳሪዎችን ማዘጋጀትና ቅድመ ሙከራ ማድረግ

የተግባቦት ፕሮግራም ስትራቴጅክ ዲዛይን ዝግጅት እንደተጠናቀቀ ዝርዝር የመርጃ መሳሪዎች ዝግጅት ይጀመራል፡፡ በአጠቃላይ የጤና ተግባቦት መርጃ መሳሪያዎችን ለማዘጋጀት የሚከተሉት ደረጃዎች ወሳኝ ናቸው፡፡

### *ንድፈ-ሃሳብ ማዘጋጀት*

በስትራቴጅው ውስጥ የተገለፁ ቁልፍ ጥቅሞችና ተፈላጊ ባህሪያት በተመረጠው የመልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴ እንዴት መቅረብ እንዳለበት መወሰን እና በተመረጠው የማስተላለፊያ ሚዲያ መሰረት የመጀመሪያ ስክሪፕት(ጽሁፍ) መምረጥ ይቻላል፡፡ በዚህ ጊዜ ጠቃሚ ምስሎችን መምረጥ (ስቶሪ ቦርድ መዘጋጀት አለበት)፡፡

ከፕሮጀክቱ ተባባሪዎች ማለትም የጤና ተግባቦት ወይም የሚዲያ ባለሙያዎች ጋር ለመግባባት ግልጽ መልዕክቶች ለማዘጋጀት የሚረዳ ንድፈ ሃሳብ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ (አባሪ 4 ይመልከቱ) ማንኛውም የተግባቦት መርጃ መሳሪያ ሲዘጋጅ ይዘቱን ከታላሚው አንጻር ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ ውጤታማ የተግባቦት ባለሙያዎች ሁልጊዜ እራሳቸውን በታላሚው ቦታ አስቀምጠው ያያሉ፡፡

እንዲሁም የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎች በሚዘጋጁበት ወቅት የሚከተሉትን መርሆች መከተል ያስፈልጋል።

## ሀ. በራሪ ወረቀቶችና የመረጃ መፅሃፍት

- የውይይት ሃሳቡን በትክክል የሚገልጽ ርዕስ መምረጥ
- ተገቢ የሆነ የአፃፃፍ ስልት መለየት፡ ይህንንም ለማድረግ ቅፆችን መጠቀም ለምሳሌ ጥያቄና መልስ፣ ማብራሪያ ፣ ትረካ፣ ወዘተ...
- መፃፍ ከመጀመር በፊት ማውጫ ማዘጋጀት
- የመልዕክቱን ዋና ሀሳብ ማስተዋወቅ
- ሀሳቦችን ለማስረዳት ስዕሎችን መጠቀም፤ ስዕሎቹንም ከሚገልፃቸው ፅሁፍ አጠገብ ማስቀመጥ
- ቋንቋው የታላሚያንን የዕውቀት ደረጃ ከግምት ውስጥ ያስገባ፣ ቀላልና ለመረዳት የማያዳግት መሆን አለበት
- በእያንዳንዱ የሀሳብ ዝርዝር ፊት ለፊት ነጥቦችና ምልክቶችን መጠቀም ይቻላል
- ታላሚውን መሰረት ያደረገ የተወሰኑ መረጃዎችን ማቅረብ አለበት
- ርዕሱ፣ ወሩ፣ ዓመተ ምህረቱ እና የተሰራበት ቦታው እንዲሁም የመርጃ መሳሪያዎች እንዲዘጋጁ ድጋፍ ያደረጉ አካላት መጠቀስ አለባቸው
- ሰዎች ተጨማሪ መረጃዎችን እንዲያገኙ ከጀርባው አድራሻ መግባት አለበት

ልዩ ዝግጅቶችን የሚያስተዋውቁ በራሪ ወረቀቶች የሚከተሉትን ነጥቦች መያዝ አለባቸው፡-

- የዝግጅቱን ስም
- ቀኑን
- ሰዓቱን
- ቦታ
- ዝግጅቱን ያዘጋጀው ድርጅት፤ ዝግጅቱ ያስፈለገበት ምክንያት

## ለ. ፖስተር

- በአንድ ፖስተር ላይ አንድ ሃሳብ ብቻ ቢተላለፍ የተመረጠ ነው፡፡ ሃሳቦች በበዙ ቁጥር ፖስተሩ ለዕይታ የማይማርክና ተመልካችን ግራ የሚያጋባ ይሆናል፡፡ ብዙ ሃሰቦችን ለማስተላለፍ ከተፈለገ ፍሊፕ ቻርት መጠቀም የተሻለ ነው

- የስዕል መግለጫዎች በምንጠቀምበት ጊዜ መግለጫው ከሰባት ቃላት ያልበለጠ መሆን አለበት
- ሁሉም ቃላት ታላሚዎች በሚናገሩት ቋንቋ መሆን አለባቸው
- የምንጠቀምባቸው ቃላት ውስንና ቀላል መሆን አለባቸው
- ምልክቶችን የምንጠቀም ከሆን ምልክቶቹ ታላሚዎች  በቀላሉ ሊረዷቸው የሚችሉ መሆን አለባቸው
- የምንጠቀምባቸው ቀለሞች እርስ በርሳቸው የሚጣጣሙ እና በተቻለ መጠን ለታላሚው ትርጉም የሚሰጡ መሆን አለባቸው
- ምስሎቹ ታላሚያን በቀላሉ ሊገነዘቧቸው የሚችሉ መሆን አለባቸው
- የሰው ምስሎችን በምንጠቀምበት ጊዜ ምስሎች የታላሚ ቡድኑን የሚወክሉ መሆን አለባቸው
- የምንጠቀማቸው ስዕሎች በታላሚው ዘንድ የተለመዱና ተቀባይነት ያላቸው መሆን አለባቸው
- አጠቃላይ ፖስተሩ ለመረዳት ቀላልና ግልጽ መሆን አለበት

የልዩ ዝግጅት ማስታወቂያ ፖስተሮች የሚከተሉትን ነጥቦች መያዝ አለባቸው፡-

- የዝግጅቱ ስም
- ቀን
- ሰዓት
- አድራሻ
- የዝግጅት ቦታ
- የዝግጅቱ ስፖንሰር

## ሐ. ቢል ቦርድ

- ብዙውን ጊዜ ቢልቦርዶ  የሚጠቅመው  በሌሎች የመልዕክት ማስተላለፊያ መንገዶች እየተላለፈ ያለን መልዕክት ለማጠናከር ነው
- በቢልቦርድ ላይ ብዙ ቃላትን መጠቀም የለብንም፤ ከሁለት ዓረፍተ ነገሮች ሙብለጥ የለበትም
- አጭር ግልጽ አሳማኝና ለማስታወስ ቀላል  በሆነ ቋንቋ መጠቀም አስፈላጊ ነው
- በጣም የሚስቡ ፎቶዎችን ወይም ምስሎችን መጠቀም ተገቢ ነው
- ከርቀት ለማየት እንዲቻል ትልልቅ ፅሁፍና ምስሎችን መጠቀም ያስፈልጋል
- የቢል ቦረዱ ይዘት ከፖለቲካና ከባህል ጋር የሚጣጣም መሆን አለበት

## መ. ፍሊፕ ቻርት

- ፍሊፕ ቻርቶች የአመቻቹን መምሪያ ወይም ሌሎች የጤና ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ለመደገፍ ይዘጋጃሉ
- እያንዳንዱ ፍሊፕ ለተጠቃሚና ለአገልግሎት ሰጭዎች የሚሆን ሁለት ገጾች መያዝ አለበት፡፡ እንዲሁም በተጠቃሚው በኩል ያለው ገጽ የበለጠ ግልጽ እና በስዕል የተደገፈ መሆን ይገባዋል
- እያንዳንዱ የቻርቱ ገፅ አንድ ሃሳብ ብቻ መያዝ አለበት
- በተቻለ መጠን ፍሊፕ ቻርቶች ታላሚዎችን ለውይይት የሚጋብዙ መሆን አለባቸው
- ምስሎቹ በታሪኩ ላይ የተመሰረተ ምክንያታዊ ቅደም ተከተል መያዝ አለባቸው
- የሚመረጡት ቃላት ቀላል እና አጭር መሆን አለባቸው
- ቁልፍ መልዕክቶች ከሌሎቹ ይልቅ ጎልተው እንዲታዩ በደማቁ መፃፍ አለባቸው
- የቻርቶች ቁጥር 5 ቢሆን ይመረጣል፡፡ ሀሳቦች በጣም በበዙ ቁጥር ሰዎች ሁሉንም ላያስታውሱ ይችላሉ
- እያንዳንዱን ቻርት በላይኛው ጫፍ አንድ ላይ ማያያዝ ያስፈልጋል
- ፍሊፕቻርቶች የጤና ባለሙያውና ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸው ስለሆኑ ለረጅም ጊዜ የሚያገለግሉ እና ለመያዝ ምቹ መሆን አለባቸው
- የፍሊፕ ቻርቶቹ የገጽ ብዛትና መጠኑ የሚጠቀሙትን የማህበረሰብ ክፍሎች ያገናዘበ መሆን አለበት

## ሠ. ምስለ-ወድምፅ የመርጃ መሳሪያዎች

- ፕሮግራሙ ከመተላለፉ በፊት ርዕሱን እንዳስተዋወቅን አጠር ያለ የመግቢያ ሙዚቃ ማቅረብ ያስፈልጋል
- በተቻለ መጠን ሙሉ ቀረፃውን ማሳጠር እና ተመሳሳይ ሃሳቦችን አለመደጋገም
- ታላሚዎች በቀላሉ ሊገነዘቡት የሚችሉት ቀላል ቋንቋ እና ቀላል የዓረፍተ ነገር አወቃቀር መጠቀም
- አሻሚ ቃላትን ማስወገድ፤ ለታላሚያን ያልተለመዱ ቃላትን ማብራራት
- ስክሪፕቱ ሲሰራ አንድን ሰው ለማነጋገር እንደሆነ ታሳቢ መደረግ አለበት
- በተቻለ መጠን ሁለትና ከሁለት በላይ ትርጉም ያላቸውን ቃላት አለመጠቀም

## ረ. ማህበራዊ ሚዲያ

- የማህበራዊ ሚዲያ ለመጠቀም በምንወስንበት ጊዜ ለታላሚው ተስማሚ መሆኑን እና ታላሚው የኢንተርኔት(በይነ - መረብ) አገልግሎት የሚያገኝ መሆኑን እርግጠኛ መሆን አለብን
- መልዕክቱን ለማጠናከር የተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን አይነቶችን መጠቀም
- የማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም ታላሚዎችን ለውይይት የሚጋብዙ ሃሳቦችን ማስተላለፍ እንዲሁም ወደ ሌሎች የመረጃ ማሰራጫዎች እንዲዛመት ማስቻል
- ታላሚዎች ሊረዱት የማይችሉት እና ትርጉም የማይሰጡ ቃላትን አለመጠቀም
- የማህበራዊ ሚዲያ ውይይቶችን ገንቢ እና ውጤታማ እንዲሆኑ የሌሎችን ሃሳብ በማይገደብ መልኩ መምራት
- በማህበራዊ ሚዲያ የምናስተላልፋቸው መልዕክቶች በቀላሉ ለብዙ ህብረተሰብ ክፍል የመድረስ እድል ስላላቸው ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል

### *ንድፈ ሃሳብን ቅድመ ሙከራ ማድረግ*

ሁሉም የጤና ተግባቦት መርጃ መሳሪያዎች ከመሰራጨታቸው በፊት ቅድመ ሙከራ መስራት አለበት ቅድመ ሙከራ ማድረግ ታላሚው መልዕክቱን በአግባቡ መረዳቱን እንዲሁም መልዕክቱ ሳቢ እና ተቀባይነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡

ንድፈ - ሃሳቡ እና የመርጃ መሳሪያው ትክክለኛ እና ከታላሚው ጋር የሚስማማ መሆኑን ለማረጋገጥ ከታላሚው እና በህብረተሰቡ ተሰሚነት ካላቸው አካላት ግብረ መልስ መቀበል ያስፈልጋል፡፡ በተገኘው ግብዓት መሰረትም የመርጃ መሳሪያውን እንደገና መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡

በቅድመ ሙከራ ወቅት ስነ አዕምሮአዊ (የመረዳት፣ ምክንያታዊ መሆናቸው፣ ተአማኒነቱን ወዘተ) እንዲሁም ተጽዕኖ ማሳደር የሚችል ( ሳቢ መሆኑን፣ ስሜት የሚቀሰቅስ፣ ባህልና ወግን የጠበቀ መሆኑን...) መመልከት ያስፈልጋል፡፡

### **የቅድመ ሙከራ ዘዴዎች**

በአብዛኛው የተለመዱት የቅድመ ሙከራ ዘዴዎች የግለሰብ ቃለ-ምልልስ እና የቡድን ተኮር ውይይት ናቸው፡፡

*የግለሰብ ቃለ ምልልስ፡-* አንድ ለአንድ የሚደረጉ ቃለ ምልልስ ሲሆኑ ውይይቱ በአንድ ጠያቂና በአንድ ታሳታፊ መካከል ሚስጠር በተጠበቀ ሁኔታ ይካሄዳል፡፡

*የቡድን ውይይት፡-* የተወሰኑ ሰዎች (8-10) በቡድን የሚወያዩበት መድረክ ሲሆን መርጃ መሳሪያዎች ወይም መልዕክቶች በቡድን ውይይት ይደረግባቸዋል፡፡

ቅድመ ሙከራ በሚካሄድበት ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

- ለቅድመ ሙከራ ወደ መስክ ከመሄዳችን በፊት የተሳታፊዎችን እድሜ፣ ጾታ፣ ልምድ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ሃይማኖትና ሌሎች የስነ ህዝብ መገለጫዎች ማወቅ፡- የቅድመ ሙከራ ናሙናው እነዚህን የስነ ህዝብ መገለጫዎች ማንጸባረቅ አለበት፡፡
- የቅድመ ሙከራ ናሙና መጠን መወሰን፡- ለእያንዳንዱ የተግባቦት መርጃ መሳሪያ የናሙና መጠን ከ50 ያልበለጠ ቢሆን ይመረጣል፡፡
- ቅድመ ሙከራ በሚካሄድበት ጊዜ የተሳታፊዎችን መልስ የተለያየ እንዲሆን ለማድረግ በአንድ ውይይት አንድ ወይም ሁለት መርጃ መሳሪያዎችን ብቻ ማሳየት ያስፈልጋል፡፡
- ለውይይት የሚጋብዙ ጥያቄዎችን መጠቀም፤

ቅድመ ሙከራ ከተሰራ በኋላ በውጤቱ መሰረት ጽሁፎችን፣ ሙዚቃውን ፣ ስዕላዊ መግለጫዎችን እና ንግግሮችን ወ.ዘ.ተ ማስተካከያ ማድረግ፤ በማሻሻያው ላይ ከመጀመሪያው የተለየ ከፍተኛ ለውጥ ከተደረገ የመርጃ መሳሪያውን በድጋሚ የቅድመ ሙከራ መሰራት፤ (በቡድን ተኮር ውይይት ቅድመ ሙከራ ለማድረግ አባሪ 4 ይመልከቱ)

### *ቅድመ ሙከራ ከተካሄደ በኋላ የመጨረሻውን መርጃ መሳሪያ ማዘጋጀት*

መርጃ መሳሪያዎች በሚዘጋጅበት ጊዜ የሚከተሉትን ቁልፍ ሃሳቦች ማካተቱን ማረጋገጥ አለብን፡፡

1. ትኩረት የሚስብ
2. መልዕክቱን በአግባቡ የሚገልፅ
3. የመልዕክቱን ጥቅም የሚያንጸባርቅ
4. መልዕክቱ የማይጣረስ
5. የታላሚውን ቀልብ የሚገዛ
6. ተዓማኒ የሆነ

7. ታላሚውን ወደ ተግባር የሚያስገባ

የዝግጅት ሂደቱ የሚሰራው ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች ማለትም የግራፊክስ ዲዛይነሮች፣ የፊልም አዘጋጆች፣ የሬዲዮ ፕሮዲዩሰሮች እና ሌሎችም ነው፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች እንዲያዘጋጁ የተጠየቁትን የተግባቦት መርጃ መሳሪያ በግልጽ እንዲረዱት ሊተላለፍ ስለተፈለገው መልዕክት የሚገልጽ ማብራሪያ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ (የፈጠራ ሃሳብ ማቅረቢያ ቅጽ ለማየት አባሪ 5 ይመልከቱ)

የጤና ተግባቦት መርጃ መሳሪያዎች እንደ አካባቢው ነባራዊ ሁኔታ በቀጥታ ሊተረጎሙ ወይም የይዘትና የቅርጽ ለውጥ በማድረግ ሊሻሻሉ ይችላሉ፡፡ እነዚህን ለማድረግ ከመረጥን፡-

- እያንዳንዱን መልዕክት በተናጠል ቅድመ ሙከራ ማድረግ
- ስዕሉንና እያንዳንዱን መልዕክት በተናጠል ቅድመ ሙከራ ማድረግ
- ቃለ ምልልስ የሚደረግለትን ሰው በማናገር ስለሚከተሉት ጉዳዮች ማወቅ፡-
    - እያንዳንዱን መልዕክት መረዳቱን/ቷን
    - የበለጠ ግልጽና ተቀባይነት እንዲኖረው መቀየር ያለበት ጉዳይ ስለመኖሩ
    - ግቡን ለማሳካት የሚያስፈልጉ ሁሉንም መረጃዎች የያዘ ስለመሆኑ
    - ምን ዓይነት የተለመዱ ቃላት መጠቀም እንዳለብን

## 2.4. የትግበራና ክትትል ሂደት

የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፣ የክልል ጤና ቢሮ ወይም አጋር ድርጅቶች እንደአስፈላጊነቱ የጤና ማበልጸግና ተግባቦት መርጃ መሳሪያዎችን ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡ ሁሉም የጤና ማበልጸግ እና የተግባቦት መርጃ መሳሪያዎች በሚዘጋጁበት ወቅት ይህንን መመሪያ መከተል አለባቸው፡፡

ሁሉም የመርጃ መሳሪያዎች በፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስተር ጤና ትምህርትና ጤና ማበልፀግ ኬዝ ቲም ወይም በሚመለከተው የክልል ጤና ቢሮ መዋቅር ወይም ለሁለቱም ቀርበው መገምገም አለባቸው፡፡

የመርጃ መሳሪያዎችን ለመገምገምና ለማጽደቅ የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጤና ትምህርትና ጤና ማበልፀግ ኬዝ ቲም / የክልል ጤና ቢሮ የሚመለከተው ኬዝ ቲም ከቴክኒካል ወርኪንግ ግሩፕ ጋር ሊሰሩ ይችላሉ፡፡

መልዕክቶች ወጥነት ያላቸው እና ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ከተለያዩ ዘርፍ መስሪያ ቤቶችና ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ትብብር የመምራት ሚና ጤና ትምህርትና ጤና ማበልፀግ ኬዝ ቲም ይወስዳል፡፡

ኬዝ ቲሙ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባባር ለሚመለከታቸው አካላት ማለትም የጤና ማበልጸግና ተግባቦት መርጃ መሳሪያዎቸ ለሚያዘጋጁ ሁሉም ዘርፍ መስሪያ ቤቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ይሰጣል፡፡

የማህበራዊ ስነ ባህርይ ለውጥ ተግባቦት ስልጠናዎችም በየደረጃው ባለው መዋቅር ይወርዳሉ፡፡ መደበኛ እና ትክክለኛ ክትትል ማድረግ መመሪያው በታቀደው መሰረት መሄዱን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡ በክትትል ወቅት ያልተጠበቁ ችግሮች እና አጋጣሚዎች ከታዩ እንደ አስፈላጊነቱ ፈጣን ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

የክትትልና የግምገማ ስርዓቱ የሚከተሉትን ነጥቦች መያዝ አለበት

- የተዘጋጀው የመርጃ መሳሪያ መመሪያውን የተከተለ መሆኑን
- የመርጃ መሳሪያዎች በሚመለከተው የፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የክልል ጤና ቢሮ መዋቅር ተገምግመው ያለፉ መሆኑን
- በሌሎች ዘርፍ መስሪያ ቤቶች ማለትም በግብርና፣ በትምህርት፣ በውሃ የተዘጋጁ ተዛማች የሆኑ የመርጃ መሳሪያዎች ደረጃውን የጠበቀ መስፈርት እና ሂደት የተከተሉ መሆናቸውን

# አባሪ 1፦

## የማኅበራዊ ባህርይ ለውጥ የተግባቦት ንድፊ ሐሳቦች

የተለያዩ የጤና ተግባቦት ስልቶችን ለመተግበርና ለመቀየስ እንዲሁም በጤና አገልግሎት ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት ብዙ አይነት የማኀበራዊ ባህርይ ለውጥ ንድፈ ሃሳቦችን እንጠቀማለን፡፡ እነዚህ ንድፈ-ሃሶቦችና ሞዴሎች ጤናማ ባህርያት ለማምጣት የሚያስችሉ ውጤታማ የሆኑ ስልቶችን ለመግለጽ ብሎም ለማዘጋጀት ይጠቅማሉ ፡፡ የማኀበራዊ ባህርይ ለውጥ ለማምጣት የሚጠቅሙ ብዙ አይነት ንድፈሃሳቦችና ሞዴሎች ያሉ ሲሆን ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### *ጤናማ እምነት ሞዴል (Health Belief Model)*


ጤናማ እምነት ሞዴል የተዘጋጀው በ1950ዎቹ ሲሆን ዋናው ጥቅሙም ሰዎች የቅድመ መከላከል አገልግሎቶችን ለመጠቀም ወይም ላለመጠቀም ምክንያት የሆኑትን ነገሮች ለይቶ ለመረዳት ነው፡፡ ይህ ሞዴል በዋናነት ታሳቢ ያደረገው አዳዲስ ክስተቶችን የመከላከልና የመለየት እንዲሁም የአኗኗር ዘዴ ባህርያትን ለምሳሌ የጾታዊ አጋላጭ ሁኔታዎችን እና አደጋ መከላከልን ለመግለጽ ነው፡፡ የጤናማ እምነት ሞዴል ንድፈ ሃሳብ የሰዎች ድርጊት በቀጥታ የሚገናኘው ለጤና ችግር መጋለጥ ወይም አለመጋለጥ ካላቸው እምነትና  ከጤና ችግሩ አስከፊነት አንጻር ባላቸው  የመረዳት ደረጃ ነው፡፡ ይህ ሞዴል አብዛኛውን ጊዜ ተግባራዊ የሚሆነው ከመከላከል ጋር ተያያዥነት ላላቸው የጤና ጉዳዮችና አጋላጭ ሁኔታዎችን ለመቀነስ ጠቃሚነታቸው በግልጽ ለታወቁ ተግባራት ነው፡፡

### *ሂደታዊ የለውጥ ሞዴል (Trans theoretical model)*

በዚህ የንድፈ ሀሳባዊ ሞዴል መሰረት የረጅም ጊዜ ለውጥ በጤናማ ባህርያት ላይ የሚመጣው በየጊዜው ተደጋግመው በሚከናወኑ ድርጊቶችና ልምዶች ነው። አንዳንድ ሰዎች የጤናማ ባህርያትን ለውጥ ለማምጣት ሙከራ የማያደርጉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ለውጡን በመተግበር ልምድ ያደርጉታል። (ለምሳሌ ሲጋራ ማጨስ፤ኮንደም አጠቃቀም ወዘተ)፡፡የሂደታዊ የለውጥ ሞዴል ጤናማ የባህርይ ለውጥ የሚመጣው ቀስ በቀስ በሂደት ሲሆን ሰዎቹም ጤናማ ባህርይውን ለመላመድ በተለያዩ የዝግጁነት ሂደቶች እንደሚያልፉና በየሂደቶቹም የተለየዩ  ተግባራት ማከናወን እንደሚያስፈልግ ያስቀምጣል፡፡

ይህ ሞዴል በአምስት ዋና ዋና ደረጃዎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ እነሱም፡-

1. ቅድመ ማሰብ፡- ይህ ሂደት ሰዎች ስለ ችግሩ ምንም አይነት ግንዛቤ ሳይኖራቸው የሚመደቡበት ደረጃ ነው
2. ማሰብ፡- ይህ ሂደት ሰዎች ስለ ችግሩና ስለ ተገቢው ጤናማ ባህርይ ሲያውቁና ማሰብ ሲጀምሩ ነው
3. መዘጋጀት፡- ሰዎች ጤናማውን ባህርይ ለመተግበር ፍላጎት ሲኖራቸው(ሲዘጋጁ)
4. መተግበር፡- ሰዎች ጤናማውን ባህርይ ተግባራዊ ማድረግ ሲጀምሩ
5. ዘላቂ ማድረግ፡- ሰዎች ጤናማ የሆነውን ባህርይ በዘላቂነት (ከ6 ወር በላይ ) ሲተገብሩ




Sources: Grimley 1997 (75) and Prochaska 1992 (148)

## *የማኀበራዊ ግንዛቤ ንድፈ ሐሳብ (social cognitive Theory)*

ይህ ንድፈ ሃሳብ የሰዎችን ጤናማ ባህርይ በሶስት መንገዶች የሚገልጽ ሲሆን እነርሱም በግለሰቦች ሁኔታ ተለዋዋጭነት ፤ በአካባቢያዊ ተጽዕኖ እና በባህርያት መካከል በሚፈጠር ተከታታይ መስተጋብር ነው፡፡ የማህበራዊ ግንዛቤ ንድፈሐሳብ ሃሳቦችና ሂደቶች የሚያተኩሩት በአዕምሮዓዊ ፤በስነ ባህርይ እና በስሜታዊ ለውጦች ላይ ሲሆን በዋናነት ተግባራዊ የሚሆነው በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረጉ የማማከር ስራዎች ላይ ነው፡፡የዚህ ንድፈ ሃሳብ መሠረታዊ መርሖች ሰዎች የሚማሩት ከራሳቸው ልምድ ብቻ ሳይሆን የሌሎችን ሰዎች ድርጊትና የድርጊቱንም ውጤት በመመልከት ነው፡፡

## *የፈጠራ/ግኝት ስርጭት ንድፈ ሐሳብ (Diffusion of innovative)*

የፈጠራ/ግኝት ንድፈ ሐሳብ በዋናነት የሚጠቅመው አንድ አዲስ ሐሳብ እና ስልጣኔ/ቴክኖሎጅ እንዴት፣ ለምንና በምን ያህል ፍጥነት ወደ ማኀበረሰብ እንደሚሰራጭ ለመግለጽ ነው፡፡በዚህ ንድፈ ሐሳብ መሰረት የአንድ አዲስ ግኝት ስርጭት በአራት ዋና ዋና ሁኔታዎች ይወሰናል፡፡ እነርሱም፡-

1. ግኝቱ/አዲስ የተፈጠረው ሐሳብ ምንነት
2. የተግባቦት መንገድ
3. ጊዜ
4. ማኀበራዊ ሥርዓት ናቸው

አንድ ፈጠራ/ግኝት ተግባራዊነቱ በማኅበረሰብ ዘንድ ዘላቂነት እንዲኖረው የብዙኃኑን ወሳኝ የሚባሉ ባህርያትን መላመድ አለበት፡፡ ከግኝቱ ጋር የሚላመዱት ግለሰቦችም በተለያዩ ቡድኖች ማለትም ግኝቱን ፈጣሪዎች፣ለግኝቱ በቶሎ የሚላመዱ፣አብዛኛውን ቁጥር የያዙና በቶሎ የሚላመዱ፣አብዛኛውን ቁጥር የያዙና ዘግይተው የሚላመዱ እና ለግኝቱ እውቅና የማይሰጡ ተብለው ይከፈላሉ፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ንድፈ ሐሳብ መርሕ መሰረት ከላይ የተጠቀሱት ዋና ዋና ክፍሎችም የሚከተለውን መጠናዊ አገላለጽ ይወክላሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. ግኝት ፈጣሪዎች-----2.5%
2. ለግኝቱ በቶሎ የሚላመዱ----13.5%
3. ቶሎ በመላመድ አብዛኛውን ቁጥር የሚወክሉ----34%
4. ቶሎ ባለመላመድ አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙ---34%
5. ለግኝቱ እውቅና የማይሰጡ-----16%

## *የማኅበራዊና ሥነ ምኅዳራዊ ሞዴል (socio ecological model)*

የማኅበራዊ እና ሥነ ምኅዳራዊ ሞዴል የሚጠቅመው የሰው ባህርይ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮችን ለመረዳትና በማኅበራዊ አካባቢ ውጤታማ የሆኑ መርሐ ግብሮችን በማዘጋጀት አቅጣጫ ለመጠቆም ነው፡፡ ይህ ሞዴል የሚያተኩረው በሰው ልጅ ባሕርይ ላይ በተለያዩ ደረጃዎች ተጽዕኖ በሚያሳድሩ ሁኔታዎች (ለምሳሌ፦ግለሰብ፣ ሰው ከሰው በሚያደርገው ግንኙነት፣ድርጅት፣ማኅበረሰብ እና የኅብረተሰብ ወግና ልማድ፤ተግባር ላይ ያሉ ህግና ደንቦች) እና የሰውን ባሕርይ በሚቀይሩና በማኅበራዊ አካባቢ በሚቀየሩ ሐሳቦች ላይ ነው፡፡ የማኅበራዊ እና ሥነ-ምኅዳራዊ ሞዴል መሰረታዊ መርሖዎች ከማኅበራዊ ግንዛቤ ንድፈ ሐሳብ መርሖዎች ጋር ተደጋጋፊነት ያላቸው ሲሆን ይህም ጤናማ ባህርያትን ለመላመድ ለባህርይ ለውጥ ምቹ የሆነ አካባቢን መፍጠር ከምንም በላይ ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

# አባሪ 2፡-

## የተመረጡ የብዙኃን መገናኛ አይነቶች ጥንካሬና ድክመት

| የብዙኃን መገናኛ ዓይነት | የአሳታፊነት አቅምና የሁለትዮሽ ተግባቦት | ጥንካሬ | ድክመት |
|---|---|---|---|
| ቴሌቪዥን | መርሐ ግብሩ አሳታፊ እንዲሆን ተደርጎ ከተዘጋጀ ብቻ (ለምሳሌ የቀጥታ ጥሪ በትዕይንቶች ወቅት) | • ሰፊ ተደራሽነት ያለው መሆኑ<br>• ከፍተኛ ደረጃ ያለውና ተዓማኒ መሆኑ<br>• ምስልና ድምጽ (መስማትና ማየት መቻሉ)<br>• ለቀላል መልዕክቶችና መፈክሮች ተስማሚ መሆኑ<br>• ግንዛቤ ፤ ዝንባሌና ደስታ እንዲገኝ መርዳቱ | • ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቅ መሆኑ<br>• መርሐ ግብሩ ሁልግዜ ለታላሚው ምቹ በሆነ ሰዓት የማይተላለፍ መሆኑ<br>• ዝቅተኛ የቴሌቪዠን ሽፋን በቤተሰብ ደረጃ መኖሩ<br>• የሚደረገው የመረጃ ልውውጥ አሳታፊ አለመሆኑ (በቴሌቪዥን ቀጥታ ስርጭት ካልተላለፈ በስተቀር) |
| ሬዲዮ | መርሐ ግብሩ አሳታፊ እንዲሆን ተደርጎ ከተዘጋጀ ብቻ (ለምሳሌ የቀጥታ ጥሪ በትዕይንቶች ወቅት) | • ከፍተኛ ተዳራሽነት ያለው<br>• ከፍተኛ ሁኔታ(ደረጃ) ያለው<br>• ለቀላል መልዕክቶችና መፈክሮች ተስማሚ የሆነ<br>• ግንዛቤ ፤ ዝንባሌና ደስታ እንዲገኝ መርዳቱ<br>• በአንጻራዊነት ሲታይ ርካሽ መሆኑ(ከቴሌቪዝን ጋር ሲወዳደር) | • ፕሮግራሙ ሁልግዜ ምቹ በሆነ ሰዓት የማይተላለፍ መሆኑ<br>• የሚደረገው የመረጃ ልውውጥ አሳታፊ አለመሆኑ (በሬዲዮ ቀጥታ ፕሮግራም ካልተደወለ በቀር)<br>• ድምጽ ብቻ የሚሰማ መሆኑ (የምስል ስርጭት አለመኖሩ) |
| ፖስተር | ግብረ መልስ ለመስጠት እድል አይሰጥም | • ቀላል መልዕክቶችና መፈክሮችን ለማስተላለፍ ተስማሚ መሆኑ<br>• ለማዘጋጀት ርካሽ መሆኑ<br>• መልዕክቶቹ ለረጅም ጊዜ መቆየት የሚችሉ(እንደገና ሊገመገሙና በድጋሚ ሊነበቡ መቻላቸው)<br>• መልዕክቱን አንባቢዎች በሚመቻቸው ጊዜ እንዲያገኙት መርዳቱ | • የማንበብና መጻፍ ለሚችሉ ሰዎች ብቻ የተዘጋጀ መሆኑ<br>• በአጠቃላይ ለቀላል መልዕክቶችና መፈክሮች ብቻ ተስማሚ መሆኑ<br>• ለቆሻሸ ፤አቧራና ጸሃይ ወዘተ የመጋለጥ እድሉ ከፍተኛ ስለሆነ ለረጅም ጊዜ መቆየት አለመቻሉ |

| የብዙኃን መገናኛ ዓይነት | የአሳታፊነት አቅምና የሁለትዮሽ ተግባቦት | ጥንካሬ | ድክመት |
|---|---|---|---|
| ብሮሹርና በራሪ ወረቀቶች | ግብረ መልስ ለመስጠት እድል አይሰጥም | • ከፖስተር ይልቅ ብዙ መልዕክት ማስተላለፍ መቻሉ<br>• መልዕክቶቹ ለረጅም ጊዜ መቆየት የሚችሉ(እንደገና ሊገመገሙና በድጋሚ ሊነበቡ መቻላቸው)<br>• ድርጊታዊ መረጃዎችን ለማስተላለፍ መጥቀማቸው<br>• ለማዘጋጀት ብዙ ወጭ የማይጠይቁ መሆናቸው | • ስርጭቱ በተወሰኑ ቦታዎች ብቻ የተገደበ መሆኑ<br>• የማንበብና የመጻፍ ችሎታ መጠየቁ<br>• ለቆሻሽ ፤አቧራና ጸሃይ ወዘተ የመጋለጥ እድሉ ከፍተኛ ስለሆነ ለረጅም ጊዜ መቆየት አለመቻሉ |
| ቢል ቦርድ | ግብረ መልስ ለመስጠት እድል አይሰጥም | • አንድ ቁልፍ መልዕክት ወይም መፈክር ለማስተላለፍ የበለጠ መጥቀሙ<br>• በአንጻራዊነት ዘላቂ መሆኑ<br>• በግልጽ መታየቱ | • ለማዘጋጀት ከፍተኛ ወጭ መጠየቁ<br>• ለዝርዝር መልዕክቶች ተስማሚ አለመሆኑ (በአብዛኛው የማስታወስ አቅም ላላቸው ሰዎች ብቻ ይጠቅማል) |
| ጋዜጣ (መጣጥፎች) | ግብረመልስ ለመስጠት የተወሰነ ቦታ ይሰጣል | • ዝርዝር መልዕክቶችን ለመዳሰስ ጠቃሚ ነው<br>• ትልቅ ተዓማኒነት አለው<br>• መልዕክቶቹ ለረጅም ጊዜ የመቆየት አቅም አላቸው (እንደገና ሊገመገሙና በድጋሚ ሊነበቡ ይችላሉ) | • ሁሉም ታላሚዎች መልዕክቱን በነጻ አያገኙትም<br>• እንደ ቲቪ እና ሬዲዮ ብዙ ሽፋን አይኖረውም<br>• የማንበብና መጻፍ ክህሎትን ይጠይቃል |
| በይነ መረብ (ኢንተርኔት) | እርስ በርስ መረጃ ለመለዋወጥ ትልቅ ቦታ ይሰጣል | • ትልቅ የዕርስ በርስ የመረጃ ልውውጥ አለው<br>• ኮምፒውተር የመጠቀም ልምድ ያላቸውን ወጣቶች ለማግኘት ይጠቅማል<br>• ግላዊ(ሚስጥራዊ ) የሆኑ መልዕክቶችን ለመለዋወጥ በጣም ይጠቅማል<br>• ከፍተኛ ግምት(ቦታ) ይሰጠዋል | • በማህበረሰቡ ውስጥ ኮምፒውተር የመጠቀም ልምዱ አናሳ መሆን(ተደራሽነቱም የተወሰነ መሆኑ)<br>• ከፍተኛ ወጭ መጠየቁ |

| የብዙኃን መገናኛ ዓይነት | የአሳታፊነት አቅምና የሁለትዮሽ ተግባቦት | ጥንካሬ | ድክመት |
|---|---|---|---|
| በሞባይል የጽሁፍ መልዕክት መለዋወጥ | እርስ በርስ መረጃ ለመለዋወጥ ትልቅ ቦታ ይሰጣል | • ትልቅ የዕርስ በርስ የመረጃ ልውውጥ አለው<br>• ግላዊ(ሚስጥራዊ ) የሆኑ መልዕክቶችን ለመለዋወጥ በጣም ይጠቅማል<br>• ለማስታወስ በጣም ይጠቅማል | • ከፍተኛ ወጭ መጠየቁ<br>• የጹሁፍ ወይም የድምጽ ብቻ መልዕክቶችን ማስተላለፍ መቻሉ(የተፈለገውን ያክል መልዕክት ለማስተላለፍ አለመቻሉ) |
| በራሪ ወረቀቶችና ተፈላጊ መርጃን የያዙ ወረቀቶች | ግብረ መልስ ለመስጠት እድል አይሰጥም | • ከስብሰባዎችበኋላ ፣በገበያ ማዕከላት ወዘተ ማሰራጨት መቻሉ<br>• በፖስታ ሊላኩ መቻላቸው<br>• አነስተኛ ወጭ የሚጠይቁ መሆናቸው<br>• በትርፍ ጊዜ ሊታዩ መቻላቸው<br>• በቤት ደረጃ በኮምፒውተር ሊዘጋጁ መቻላቸው | • ውስን በሆኑ መልዕክቶችና በተለዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መወሰናቸው<br>• አንድ ቁልፍ መረጃ ወይም ጠቃሚ ምክር ብቻ መያዛቸው |
| የርስ በርስ ተግባቦት | እርስ በርስ መረጃ ለመለዋወጥ ትልቅ ቦታ ይሰጣል | • የተሻለ መረዳዳት ይኖራል<br>• ዝረዝር መረጃ ማግኘት ይቻላል<br>• ግላዊ(ሚስጥራዊ) መረጃዎችን ለመለዋወጥ የበለጠ ይጠቅማል | • ብዙሃኑን መድረስ አለማስቻሉ |

# አባሪ 3፡-

## የቅድመ ሙከራ የቡድን ውይይት መምሪያ

## አመቻቾች:______________________________
## ፀሃፊዎች:______________________________

## የቅድመ ሙከራው ዓላማ:

____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________

# በቅድመ ሙከራ ወቅት ሊታወሱ የሚገባቸው ጉዳዮች

- ተገቢነት(አስፈላጊነት):- መልዕክቶቹ ከችግሩ አንጻር ጠቀሜታቸውን ከመረዳትና ታላሚው የሚፈለገውን የባህርይ ለውጥ እንዳያመጣ መሰናክል ይሆናሉ ተብለው የተለዩ ችግሮችን ከመፍታት ያላቸውን ጠቀሜታ ማየት
- መረዳት:-መላሾች መልዕክቱን ምን ያክል እንደተረዱት፣ግልጽ ያልሆነላቸው ፤ ግራ ያጋባቸው ወይም ለማመን የተቸገሩበት ነገር እንዳለ ማየት
- ተቀባይነት:-መልዕክቶቹ ከአካባቢው ባህልና ልምድ አንጻር ተገቢና ተቀባይነት ያላቸው መሆኑን ለማወቅ መሞከር
- ታላሚውን የሚማርክ:- ታላሚው መልዕክቱን ተገቢና ማራኪ ነው ብሎ መቀበሉን ማየት
- ተሳታፊነት:-ታላሚው መልዕክቱን ይመለከተኛል ብሎ ማሰቡንና መረዳቱን ማየት

# ትውውቅ

እንደምን አደራችሁ/ዋላችሁ

በቅድሚያ ከኛ ጋር ለመወያየት በመምጣታችሁ አመሰግናለሁ። ስሜ _______________ ሲሆን፣ እዚህ ጋር የምትመለከቱት/ቷት የስራ ባልደረባዬ_______________ ይባላል/ትባላለች። የመጣነው _______________ ከተባለ ድርጅት ነው። ዛሬ የጋበዝናችሁ በምናዘጋጃቸው (ፖስተሮች፥ በራሪ ወረቀቶች፥ ማስታወቂያዎች፥ ፊልሞች፥ ወዘተ) አስተያየታችሁን ፈልገን ነው።

አሁን ይዘናቸው የመጣነው (ፖስተሮች፥ በራሪ ወረቀቶች፥ ማስታወቂያዎች፥ ፊልሞች፥ ወዘተ) ገና በሃሳብ ደረጃ ላይ ያሉ ናቸው። ፖስተሮቹን በማዘጋጀት ላይ እንገኛለን፡፡ እነዚህን ፖስተሮች ለህብረተሰቡ ከመድረሳቸው በፊት እናንተ ግልጽ የሆነ አስተያየታችሁን ብትሰጡን እጅግ ይረዳናልና የተሰማችሁን ከመናገር ወደኋላ አትበሉ።

ይህንን ፖስተር በተመለከተ ጥቂት ጥያቄዎች እንጠይቃችኋለን። መልስ ስትሰጡ፣ በተቻላችሁ መጠን እውነተኛ ስሜታችሁን ገልጻችሁ ተናገሩ። እናንተ የምትሰጡን አስታያየቶች በጣም ይጠቅሙናል ምክንያቱም ለሚመለከተውና ለሚያነበው ሰው በተሻለ ሁኔታ እንዲጠቅመው ሆኖ እንዲወጣ ትረዱናላችሁ።

# ሂደት 1፦ እያንዳንዱን ጥያቄዎች በየተራ ጠይቅ

1. ምን ይታይሃል/ይታያችኋል ብታስረዱን?

2. በ(ፖስተሩ፥ በራሪ ወረቀቱ፥ ማስታወቂያው፥ ፊልሙ፥ ወዘተ) ሊተላለፍ የተፈለገው ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

3. ይህ (ፖስተር፥ በራሪ ወረቀት፥ ማስታወቂያ፥ ፊልም፥ ወዘተ) ለማን የተዘጋጀ ይመስላችኋል? መልዕክቱ ይመለከተናል ብለው ስለሚያስቡ ሰዎች ምን እንደሚመስሉ ግለጹልን፡፡

4. እስቲ በዚህ (ፖስተር፥ በራሪ ወረቀት፥ ማስታወቂያ፥ ፊልም፥ ወዘተ) ላይ ስለተሰማችሁ አጠቃላይ ስሜት ግለጹልን፡፡

5. ከዚህ (ፖስተር፥ በራሪ ወረቀት፥ ማስታወቂያ፥ ፊልም፥ ወዘተ) ውስጥ የወደዱት ምንድን ነው?

6. ከዚህ (ፖስተር፥ በራሪ ወረቀት፥ ማስታወቂያ፥ ፊልም፥ ወዘተ) ውስጥ የጠሉትስ ምንድን ነው?

7. ያልገባችሁ ነገር አለ? ለምሳሌ ቃላት፣ ዓረፍተ ነገር፣ ወይንም ዋና ሃሳብ ያልተረዳችሁት አለ? ካለ፣ የትኛው? (የተፈለገውን ሃሳብ እና ትርጉም በማስረዳት ተሳታፊዎችን የተሻለ በይበልጥ የተፈለገውን ሃሳብ ወይንም ቃል የሚገልጥ አማራጭ እንዲያቀርቡ ጠይቅ/ቂ)

8. የጎደለ የሚመስላችሁና እንዲጨመር የምትፈልጉት ነገር አለ?

9. የጎደለውን ሊያሟላ ይችላል ብላችሁ ያሰባችሁት ነገር ካለ ብታካፍሉን ወይንም ሊሻሻል የሚችልበትን መንገድ ካለ ብትነግሩን፡፡

## ሂደት 2፦ ከብዙ ሃሳቦች የተሻለውን ስለመምረጥ

10. ከምታይዋቸው ሃሳቦች የትኛው በይበልጥ ይመቻል/ይስባል ብላችሁ ታስባላችሁ፡፡ (የትኛው ይመቻችኋል?)

11. ለእናንተ ህይወትና አናኗር ሁኔታ የትኛው ይቀርባል ብላችሁ ታስባላችሁ?

12. የትኛው ለመረዳት ይቀላል?

13. የትኛው እንድታስተውሉት ይገፋፋል? የትኛው ሙድ አለው?

14. የትኛው እውነተኛ ይመስላል? ለተመልካቹ የትኛው የሚታመን መልእክትን የዟል?

15. ከባህላችንስ ጋር አብሮ ይሄዳል የምትሉት የትኛውን ነው?

## ተሳታፊዎችን በማመስገን ውይይቱን መዝጋት።

# አባሪ 4፦

## የተግባቦት መልዕክቶችን ለማዘጋጀት የሚረዳ ንድፍ

| ልናዘጋጅ የምንፈልገው ንድፈ-ሀሳብ | ይዘት |
|---|---|
| 1. አጠቃላይ የተግባቦቱ አላማ | |
| 2. የሚፈለጉ ታላሚዎች<br><br>(መድረስ የምንፈልጋቸው ታላሚዎች፣ለመጀመሪያ ታላሚዎች ቅድሚያ ስጥ፤ የጤና ችግሩ ያለባቸው እና የመጀመሪያ ታላሚዎች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የመጀመሪያ ታላሚዎችን ጤናማ ባህሪያት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ) | |
| 3. እንዲመጣ የምንፈልገው ባህርይ<br><br>(ታላሚዎች መልዕክቱን ካዳመጡ ፣ከተመለከቱ ወይም ከለመዱት በኃላ ምን እዲያደርጉ እንፈልጋለን?) | |
| 4. ታላሚዎቻችን የሚፈለገውን ጤናማ ባህርይ ለመተግበር የማይችሉበት ምክንያት ምንድነው (ተግዳሮቶች)<br><br>(በታላሚዎቻችን እና እንዲተገበር በሚፈለገው ጤናማ ባህርይ መካከል ምን አይነት የተጋረጡ ሁኔታዎች አሉ( እምነት፣ ባህል፣ የጓደኛ ግፊት፣ የተሳሳተ ወይም የተዛባ መረጃ ወዘተ) | |
| 5. የሚፈለገውን ጤናማ ባህርይ ለመላመድ የማያስችሉ ተግዳሮቶች<br><br>(ከተዘረዘሩት ተግዳሮቶች ውስጥ የምንፈልገውን ጤናማ ባህርይ እንዳይተገበር ከሚያደርጉት መሰናከሎች ውስጥ ዋናውን መለየት) | |

| ልናዘጋጅ የምንፈልገው ንድፈ-ሀሳብ | ይዘት |
| --- | --- |
| 6. የተግባቦቱ አላማ በታላሚዎች እይታ (ዋና ተግዳሮቶችን መቅረፍ)<br><br>መልዕክቱን በአግባቡ ከተዘጋጀና ከተላለፈ መልዕክቱን ተግባራዊ የሚያደረጉ የመጀመሪያ ደረጃ ታላሚዎቻችን ከነበረበት ቁጥር መጨመር ይኖርበታል | |
| 7. ዘለቄታና በቀላሉ ሊታወስ ወይም ሊለይ የሚችል (የሚታወቅ መለያ)<br><br>(እንዴት አድርገን ነው ከነበሩ ወይም ከተለያዩ ዘመቻ ጋር መለያዎችን ማገናኘት የምንችለው?) | |
| 8. ስልታዊ አቀራረብ<br><br>(ምን አይነት የመገናኛ ዘዴ ስብጥሮችን ተጠቅመን ነው የምንፈልገውን የባህርይ ለውጥ ማምጣት የምንችለው?) ለምሳሌ፤ የብዙሃን መገናኛ ዋና የመልክት ማስተላለፍያ መንገድ ቢሆንም በሌላ የማህበረሰብ ንቅናቄ ስልት መደገፍ አለበት። ለምን ቢባል ለምሳሌ ሬዲዮ ብዙ የምንፈልጋቸውን ታላሚዎች ሊደርስልን ይችላል ነገር ግን በሰዎች መካከል በሚደረግ ውይይት መደገፍ አለበት) | |
| 9. የባህሪው ዋና ጥቅም<br><br>(ታላሚዎቻችን እዲተገበር የምንፈልገው ጤናማ ባህርይ ከሰሙ፣ካዩ፣ካነበቡ እና ተግባራዊ ካደረጉ በኃላ ሊያገኙ የሚችሉትን አንድ ዋና ጥቅም ከተቀመጠ ያስቀመጥነው አላማ መሳካት ይችላል)<br>ይህንን አካሄድ ተጠቅመን :-ይህንን ካደረጉ (የተግባቦቱ አላማ)______________ ይህንን ይጠቀማሉ (ጤናማ ባህርይ)______________ | |

| ልናዘጋጅ የምንፈልገው ንድፈ-ሀሳብ | ይዘት |
| --- | --- |
| 10. ደጋፊ ሀሳቦች<br><br>(እዲተገበር የሚፈልገው ጤናማ ባህርይ ተግዳሮቶች ከሚፈጥሩት ጤናማ ካልሆነ ባህርይ እንደሚበልጥ በምክንያት ማሳየት አለብን። ይህም የምንፈልገው ዋና መልዕክት ወይም መፈክር መሆን ይገባዋል<br>ይህ ከላይኛው ሀሳብ የቀጠለ ነው ስለዚህ ሲገለፅ<br><br>ምክንያቱም_________________ | |
| 11. ወደተግባር የሚያስገባ<br><br>ታላሚዎቻችን ምን እዲያደርጉ ነው የምንፈልገው ወይም የት ሄደው ነው መልዕክቶችን መጠቀም የሚችሉት? (ለምሳሌ ለበለጠ መረጃ የስልክ መስመሮች ላይ ይደውሉ__________ | |
| 12. ቁልፍ ይዘት<br><br>(ዋና ዋና ቁልፍ ሀሳቦችን በአንድ ላይ በመሰብሰብ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ) | |
| 13. ድምፀት<br><br>(መልዕክቶችን በምናቀርብበት ወቅት ድምፀቱ ምን መምሰል አለበት? (ለምሳሌ ለዘብተኛ፣አስቂኝ፣አስገራሚ፣ፈጠራ የታከለበት፣ የተለመደ ወዘተ ወይም ከላይ ያሉት ድብልቅ) | |

| ልናዘጋጅ የምንፈልገው ንድፈ-ሀሳብ | ይዘት |
|---|---|
| 14. የሚከናወኑ ተግባራት<br><br>ለታላሚዎች በተሻለ መልኩ ልናቀርብ ያሰብናቸውን ተግባራትና የተግባቦት መሳሪያዎችን ቁጥር አይነታቸውን መዘርዘር | |
| 15. መልዕክቱ የሚተላለፍበት ጊዜና ቦታ<br><br>(ምን አይነት አጋጣሚዎች አሉ? ለምሳሌ ታላሚዎችን ለመድረስ ያሉ ግዜና ቦታዎችን? ለምሳሌ የገበያ ቀን፣ የአለም ኤች አይ ቪ/ኤድስ ቀን ወዘተ) | |
| 16. ሌሎች የፈጠራ ባለሙያዎቹ ሊያውቋቸው የሚገቡ ነገሮች<br><br>(የተግባቦት መልዕክቱን የሚፈጥሩት ሰዎች ምን ተጨማሪ መረጃ ማወቅ አለባቸው? ለምሳሌ፡- ከአንድ በላይ ቋንቋ መቅረብ አለበት ወዘተ) | |

# አባሪ 5፡-

ጥራት ያለው የማህበራዊ የባህርይ ለውጥ ተግባቦት መልዕክቶችን ለማዘጋጀት የሚረዳ መዘርዝር

## መልዕክቶቹ ትክክለኛ ናቸው ወይ?

- የተግባቦት መልዕክቶቹ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ በባለሙያ ታይተው ትክክለኛነታቸው መረጋገጥ አለባቸው
- የተግባቦት መልዕክቶችና የተዘጋጁት መርጃ መሳሪያዎች የተጣጣሙ ናቸው ወይ?
- በሁሉም ተግባራትና የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ያሉ መልዕክቶች እርስ በርሳቸው የሚደጋገፍና ስትራቴጃዊ መዕቀፍን የሚከተሉ መሆን አለባቸው
- መልዕክቱ አንድ ስዕላዊ የሆነ መገለጫ ሊኖረው ይገባል ይኸውም የሚታተሙ የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ተመሳሳይ የሆነ ወይም ተመጣጣኝ ቀለሞች፣ የገለፃ አይነቶችና አቀማመጥ መጠቀም አለባቸው። ሁሉም የተግባቦት የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች በውስጣቸው የአዘጋጁን መለያ ወይም ጭብጥ ሀሳብ ከተቻለ መያዝ አለባቸው፡፡

## መልዕክቶች ግልፅ ናቸው ወይ?

- ለመልዕክቶች ቀላልና በውስጣቸው ጥቂት ሳይንሳዊና ሙያዊ ቃላትን መጠቀም አለብን
- የምናስተላልፋቸው መልዕክቶች ግልፅና አድማጮች ሊተገብሯቸው የሚችሉት መሆን አለባቸው
- የምስል የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ለምሳሌ እንደ ፎቶ ያሉ መልዕክቶች አድማጭ ላይ ተጽዕኖ በመፍጠር በቀላሉ ለመረዳትና ለማስታወስ እገዛ ያደርጋሉ

## መልዕክቶችና መርጃ መሳሪያዎች ለታላሚዎቹ ጠቃሚ ናቸው ወይ?

- መልዕክቱ እንዲተገበር የምንፈልገውን ባህርይ ታላሚዎቹም ዋጋ ሊሰጡትና የሚኖረውን ጥቅም ሊገልጽ ይገባል፡፡ ለምሳሌ ከጥቅሞቹ መካከል የስነልቦና (ስሜቶችን ለመቆጣጠር ተነሳሽነት ይጨምራል)፤ ራስ ወዳድ አለመሆን (ለምሳሌ አራርቆ መውለድ እናትና ልጅን ጤናማ ይደርጋል)፣ የተሻለ ምጣኔ ሀብት (ጥቂት ልጆች ካሉን ሁሉንም ማስተማር እንችላለን) እና ጥሩ የማህበራዊ ሀላፊነት (ኮንዶም በአግባቡ የሚጠቀሙ ብልሆች ናቸው)
- የመልዕክቱ አቀራረብ የታላሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆን አለበት። ለምሳሌ ምክንያታዊ አልያም ስሜታዊ አቀራረብ ወይም ጠንከር ያለና አልያም ቀለል ያለ አቀራረብ መሆን አለበት
- መልዕክቶች ክልላዊ ልዮነቶችን ታሳቢ ማድረግ አለባቸው ይህም ሲባል ከቋንቋ አጠቃቀም ጀምሮ እስከ ማህበረሰቡ አለባበስ ያሉትን ልዩነቶች የጤና አገልግሎት ሰጪ ተቋማትም ታስቢ ማድረግ አለባቸው

## የመልዕክት ማስተላለፊያ መንገዶቹ ታማኝ ናቸው ወይ?

- ለታላሚዎች የሚደርሱ መልዕክቶች የመረጃ ምንጫቸው ታማኝ መሆን አለበት። ለምሳሌ የጤና ባለሙያዎች ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸው ሰዎች ይበልጥ ተዓማኒነት ሊኖራቸው ይችላል
- በህብረተሰቡ ዘንድ ተፅዕኖ ፈጣሪ ወይም በንግግር ችሎታቸው የሚታወቁ ሰዎች በጥንቃቄ መመረጥ አለባቸው። የምንመርጣቸው ሰዎች ባህርይ ከሚፈለገው ጤናማ ባህርይ ጋር በቀጥታ ከመልዕክቱና ከተግባሩ ተዛማች ሊሆኑ ይገባል ለምሳሌ ሯጭ ስለ አካል ብቃት እንቅስቃሴ ቢያስተምር፡፡

## መልዕክቶችና የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ሳቢና ማራኪ ናቸውን?

- መልዕክቶች የታላሚውን ትኩረት መሳብ አለባቸው
- ተግባራትና መልዕክቶቹ ከፍተኛ ጥራት ሊኖራቸው ይገባል

## መልዕክቶችና የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የስነ ፆታ ልዩነቶች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ ወይ?

- መልዕክቶች ሲዘጋጁ የፆታ ልዩነቶች ላይ ተፅዕኖ ማሳደር የለባቸውም
- መልዕክቶችና የመርጃ መሳሪያዎች በውስጣቸው አዎንታዊ ተቀባይነት ያላቸውን ምሳሌዎች ማካተት አለባቸው

መልዕክቶች፤ የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎችና ተግባራት የወንዱንና የሴቷን ፍላጎትና ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘቡና ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው። ለምሳሌ የስራ ጫና፣መረጃና አገልግሎትን የማግኘትና የመዘዋወር ነፃነት ልዩነቶች ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው፡፡

# አባሪ 6፦

## የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የስርጭትና የትግበራ ክትትል ለማካሄድ የተዘጋጀ ፈጣን መዘርዝር

| ተግባቦታዊ ሂደት(አሰራሮች) | ትርጉምና ዝርዝር | በጣም ደካማ | በጣም መሻሻል የሚፈልጉ | በከፊል መሻሻል የሚፈልግ | በጣም ጥሩ | በቂ አቅርቦት ያለው (ምን ያህል ቅጂዎች አሉ) ምን ያህል ብዛት ለስድስት ወር ያስፈልጋል |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. ተገቢ ማስተላፊያ ዘዴ ለታላሚዎች | ታላሚዎቹ ምን አይነት የማስተላለፊያ ዘዴ ነው መረጃ ለማግኘት የሚጠቀሙት? ታላሚዎች የዚህ አይነት የማስተላፊያ ዘዴ ከዚህ በፊት ተጠቅመው ያውቃሉ ወይ? የተሰጡትን አስተያየቶች የሚያግዝ በሚዲያ አጠቃቀመም ላይ የተሰራ ጥናት አለ ወይ? | | | | | |
| 2. የታተሙ የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች የሚተላለፍበት ቦታ | የታተሙ የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ካሉ የት ነው የሚለጠፍት? የሚለጠፍበት ቦታ አብዛኛው ታላሚ በትክክል ቆሞ የሚመለከትበት ቦታ ነው ወይ? ቦታው የምንፈልገው ታላሚ በትክክል በሚያይበት ደረጃ ነው ወይ? የተለጠፉት ብዙ ህዝብ በሚገኝበት ቦታዎችና በቀላሉ ሊታይ በሚችል ቦታ ነው ወይ? | | | | | |

| ተግባቦታዊ ሂደት(አሰራሮች) | ትርጉምና ዝርዝር | በጣም ደካማ | በጣም መሻሻል የሚፈልጉ | በከፊል መሻሻል የሚፈልግ | በጣም ጥሩ | በቂ አቅርቦት ያለው (ምን ያህል ቅጂዎች አሉ) ምን ያህል ብዛት ለስድስት ወር ያስፈልጋል |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 3. የቃላት መብዛት | በመንገድ ላይ እያለፍን የምናነባቸው መልዕክቶች ከሆኑ (ይህም ማለት ብዙ ህዝብ በሚበዛበት ቦታ የሚለጠፉ ከሆነና ቤት ወስደን የማናነበው ከሆነ) በፍጥነት ለማንበብ ከተፈለገ ቃሎቹ መብዛት የለባቸዉም | | | | | |
| 4. መልዕክቶችን ለማስተላለፍ ማራኪ የሆነ የፊደል አጣጣልና ስዕላዊ አጠቃቀም | የቀለማትና ምስሎች አጠቃቀም የሚስብ ወይም የሚያሰለች ነው ወይ?ምስሎቹ በትክክልና በቀጥታ መረጃዎቹን ማስተላለፍ ይችላሉ ወይ ወይም እንዲሁ ለማሳመር ብቻ የተቀመጡ ናቸው ወይ? | | | | | |
| 5. ጥንቃቄ የተሞላበት የመረጃ አመራረጥ | የመረጥነው መረጃ የምንፈልገውን መልዕክት ለማስተላለፍ ተደርጎ በጥንቃቄ የተረመጠ ነው ወይ? በተነፃፃሪ ጠቃሚ ያልሆኑ መረጃዎች የመረጥነውን መርጃ መሳሪያ ጥቅም እንዳይኖረው ያደርጋሉ። ይህ ከሆነ መረጃ ባይተላለፍ ይሻላል | | | | | |

| ተግባቦታዊ ሂደት(አሰራሮች) | ትርጉምና ዝርዝር | በጣም ደካማ | በጣም መሻሻል የሚፈልጉ | በከፊል መሻሻል የሚፈልግ | በጣም ጥሩ | በቂ አቅርቦት ያለው (ምን ያህል ቅጂዎች አሉ) ምን ያህል ብዛት ለስድስት ወር ያስፈልጋል |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6. የቋንቋ አጠቃቀም | የምንናገራቸውና የምንፅፋቸው ቋንቋዎች (ባላቸው የክብደት መጠን፣ለትርጉም አስቸጋሪ የሆኑ፣ ብሄራዊ ቋንቋዎችን አልያም የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ብቻ የሚግባቡበት) ለመድረስ ለምንፈልጋቸው ሰዎች ተመጣጣኝ ናቸው ወይ? | | | | | |
| 7. ቀጣይ ሂደቶችን ማመላከት | መረጃዎቹ ግልጽ ከሆኑ አንባቢዎችና ተመልካቾች በመረጃው መሰረት ለምን መተግበር አልቻሉም? | | | | | |